የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

| አሥራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰ አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፪ሺ ዓ.ም. | በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 14th Year No. 48 ADDIS ABABA 1ST August 2008 |
|---|---|---|

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ

የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..............ገጽ ፬ሺ፩፻፵፬

## CONTENTS

Regulation No. 154/2008

Higher Education Cost-sharing Council of Ministers Regulation ........................................ Page 4144

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ

### ስለከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፫፻፶፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፶፮/(፫) እና አንቀጽ ፺፱ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፶፬/፪ሺ›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. ‹‹ሚኒስቴር›› ወይም ‹‹ሚኒስትር›› ማለት እንደቅደም ተከተላቸው የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

፪. ‹‹ተቋም›› ማለት በመንግሥት አካል ሥር የሚተዳደር ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ትምህርት የሚሰጥበትና በማንኛውም ክልል፣ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ውስጥ የሚገኝ ሆኖ ከፌደራል መንግሥት በሚመደብለት በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው፤

*Council of Ministers Regulation No. 154/2008*

### *A COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR HIGHER EDUCATION COST-SHARING*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 56(3) and 99 of the Higher Education Proclamation No. 351/2003.

1/ *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Higher Education Cost-Sharing Council of Ministers Regulation No. 154/2008".

2. *Definitions*

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Education, respectively;

2/ "Institution" means a public higher learning institution in any region, in Addis Ababa or Dire Dawa offering a post-secondary education with a budget allocated from the Federal Government;

ያንዱ ዋጋ Unit Price 3.40

፲፯. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

፩. ሚኒስቴሩ በሚያወጣው ልዩ መመሪያ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም የመንግሥትም ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሙያው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበትን ተመራቂ አገልግሎቱን ማጠናቀቁን ሳያረጋግጥ እንዲሁም ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ክፍያውን ሳያጠናቅቅ ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል የለበትም ::

፪. ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

፲፰. <u>የተሻረ ደንብ</u>

የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፺፩/፲፱፻፺፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል።

፲፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፪ሺ. ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

17/ *Duty to Cooperate*

1/ Unless permitted otherwise by specific directive to be issued by the Ministry any government or private higher education institution shall not accept an applicant for the further higher training before ensuring that the applicant has fulfilled the service obligations or financial duty.

2/ Every person shall have the duty to cooperate with the concerned authorities in the implementation of this Regulation.

18/ *Repealed Regulation*

The Higher Education Cost-Sharing Council of Ministers Regulation No. 91/2003 is hereby repelled.

19. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 1st day of August, 2008.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ